በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መጋቢት 30 ቀን 2011 ዓ/ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ከብሔራዊ ደህንነት ምክር ቤት የተሰጠ መግለጫ

ብሔራዊ የደህንነት ምክር ቤት በ30/07/2011 ዓ/ም በመላ ሃገራችን እየተስተዋሉ ያሉ የሰላም መደፍረሶችን በአጠቃላይ፣ በአማራ ክልል የኦሮሞ ብሔረሰብ አስተዳደርና በሰሜን ሸዋ ዞን አዋሳኝ አካባቢዎች ያለውን የሰላም መደፍረስ ደግሞ በተለየ ትኩረት በመገምገም የሚከተለውን መግለጫ አውጥቷል።

በኬሚሴ እና በአጎራባች አካባቢዎች የተከሰተው የሰው ሕይወት መጥፋትና የንብረት ውድመት በምንም አግባብ ተቀባይነት የሌለው ተግባር ነው። በግጭቱ ህይወታቸውን ላጡ፣ አካላቸው ለጎደለ እና ንብረታቸው ለወደመባቸው ሁሉ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን ምክር ቤቱ ይገልጻል።

የዜጎች በሰላም የመኖር ዋስትና እና የሕግ የበላይነት ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብ የመንግስት ዋነኛ ሃላፊነት መሆኑ ይታወቃል። የተከሰተውን የሰላም መደፍረስ ለማረጋጋትና የዜጎች ሰላም ዋስትና እንዲያገኝ የሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል የጸጥታ አስከባሪ ተቋማት አስፈላጊውን ህጋዊና ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ትዕዛዝ ተላልፏል። ብጥብጡን ያቀናበሩት፣ ያነሳሱትና የፈጸሙትን አካላት ለህግ የማቅረቡ ጉዳይ በከፍተኛ ትኩረት ይሰራበታል። ለዚህም ጥናት የሚያደርግ ቡድን ከክልሉ እና ከፌደራል ተቋማት ተሰማርቷል። በጥናቱ ውጤት መሰረት በብጥብጡ ላይ እጁ ያለበት ማንኛውም አካል በህግ ተጠያቂ እንደሚሆን ያረጋግጣል።

ከዚህም ባሻገር ችግሮች የሚከሰቱት በውስን የራሳቸው አጀንዳ ያላቸው የጥፋት ሃይሎች ሆኖ ሳለ በመደበኛውም ሆነ በማህበራዊ ሚዲያ የህዝብ ለህዝብ ግጭት የተፈጠረ በማስመሰል የማራገብ ስራ የሚሰሩ አካላትም ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡና ጉዳዩን በሰከነ፣ ሙያዊ ስነ-ምግባርን እና የሃገርን አንድነት በሚጠብቅ መልኩ እንዲይዙት ያሳስባል።

በመጨረሻም መንግስት ህግን ለማስከበርና የዜጎችን ሰላም ለማስጠበቅ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛ መሆኑንና ሕገወጥ ተግባራት ላይ የሚሳተፉ አካላት ከድርጊታቸው የማይቆጠቡ ከሆነ መንግስት ሕግን ከማስከበር ወደ ኋላ እንደማይል በድጋሚ ያረጋግጣል።

//